# ካለፈው የቀጥለ ሶሻል ሚድያ ለበጎ

ቀሲስ አስተርአየ

ሰኔ 16 ቀን 2018 ዓ/ም

"በኦርቶዶክሳውያን ካህናትና መምህራን መካከል የማሕበራዊ ሚድያ  እውቀትን፤ መግባባትን፤ አንድነትን፤ ሕሊናነትንና ሞራላዊነትን በማሳደግ  መኅበራዊ  ሚድያ ለበጎ ነገር እንዴት "ዕቃ ጦር" ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል ለማሳየት ይጥራል" ተብላ በቀረበችው መመሪያ ሶስት ጥያቄወች ተንጸባረቁብኝ።

አንደኛው፦ ሙሴ በዮቶር ጥበብ እየተመራ ሕዝቡን በ12 ቁጥር አደራጅቶ ያሻገረባትን አባቶቻችን  ምሳሌ በማድረግ በሰንበቴ በጽዋዕ ማህበራትና በመቃብያን ፈሊጥ ኢትዮጵያውያንን አደራጅተው ኢትዮጵያን ከወራሪወች ያተረፉባቸው እሴቶች ናቸው። ስለ ሰንበቴና ጽዋ ማህበራት መረዳት ከፈለጉ ከዚህ ቀደም ያቀረብኩትን ይህንን በመጫን ያንብቡ። የጽዋዕ-ማህበራት-በቀሲስ-አስተርአየ-ጽጌ

ሁለተኛው፦ ዮቶራዊውን ጥንታዊ አደረጃጀት ከክርስትና ጋራ በማዛመድ የጽዋ ማህበራትንና የሰንበቴውን አደረጃጀት በሥላሴ በመድኃኔዓለም በእመቤታን በጻድቃን በሰማእታትና በመላእክት ስም በ12 ወራት በ12 ሐዋርያትና በአራቱ ጣቶቻን 12 አጽቆቻችን ቁጥር ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ሕብረተ ሰቡን ያደራጁበት ሰበካ ጉባዔ ነው።

ሶስተኛው፦ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይዘቷን ለማጥበብ ኃይሏን ለማዳከም ከአማራው ጋራ ደርበው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ያዋቀሩት ሰበካጉባዔን የሙቱበት የወያኔወች ደባ ነው።

የጥንቱ የኢትዮጵያዊው ዮቶራዊ አደረጃጀት ሕብረተ ሰቡ ራሱን ሚድያ አድርጎ ሀዘኑንም ደስታውንም ይካፈልበት ነበር። የወጭ ወራሪወች ሲመጡ ኢትዮጵያውያን መሪወች የከተት ጥሪያቸውን የሚያስተላልፉባቸው ህዝቡም ጥሪውን እየተቀባበል ይሰለፍ የነበረው በዚሁ በዮቶራዊው አደረጃጀት በተወቀሩት ሚድያወች ነበር።

በነዚህ ሚድያነት በተላለፉት ጥሪወች የተከናወናወኑትን አስደናቂ ሕዝባውያን ድሎች የወጭ ታዛቢወች እጅግ በመደነቅ ገልጸዋቸዋል። በነዚህ ሚድያነት በተላለፉት ጥሪወች ስለተ ተከናወነወኑት አስደናቂ ሕዝባውያን ድሎች የወጭ ታዛቢወች እየጻፉ በምስክርነት ያስቀመጧቸው መረጃወቻ ባይኖርልን ኖሮ፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንና ኦርቶዶክሳውያንን ከኢትዮጵያ ገጸ ምድር ለማጥፋት ታጥቀው የተነሱት የስላቅ ፖለቲካ አራማጆች የሚያስራጩትን አወናባጅ ወናፍ አባቶቻችን ባቆዩልን ታሪክ ብቻ መቋቋም አንችልም ነበር።

ኢትዮጵያን ጠብቀው ባቆዩ አባቶቻችንና  በጠበቁባቸው እሴቶች ላይ ታጥቀው የተነሱት ጥሪዝ ነጥቆች የምንናገረውን ካፋችን እየለቃቀሙ ቆርጠው ጠማማ ስላቃቸውን በመቀጠል ሙሉ መልእክታችን ላልደረሰው ሕዝብ እኛን አከፍተው በማቅረብ እያስጠሉን ሕዝባችንንም በማደናበር ላይ ናቸው። ስለ ሶሻል ሚድያ የምናገርባትን ይህችን ጦማር ሳቀርብ እነዚሁ ቀበያውባጢወች ቆርጠው ቀጥለው ማቅረባቸውን ከወዲሁ ለመከላከል የውጭ ሰወች የመሰከሩትን እጠቅሳለሁ።

ስለኛ ብዙ ከጻፉ ሰወች ለምሳሌ Drusilla Dunjee Houstin የተባሉ ጸሐፊ "wonderful Ethiopians of the Ancint cushite empire" በሚል እርእስ የሰጡትን ምስክርነት እንመልከት። የራሳቸውን ምስክርነት እንዲሰጡ እኒህን ጸሐፊ የገፉቸው ከሳቸው በፊት ቀደም ብሎ የነበረ Heeren  የሚባል የታሪክ ጸሐፊ የሰጠውን ምስክርነት መሠረት አድርገው በመጠቀስ ነበር።

Houstin እንዲህ ይላሉ። Heeren, Whose reserhes furnish invalable information to the later days, "From the remotest  times to the present, the Ethiopians have been the moste celebred  and yet the most myysrious of nations. In the earlirst tradations of the more  civilized  nations of antiquity, the name of the most distant people is found"(pqge 24) ይህ ምስክርነት በዚህ ዘመን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ይልቁንም ኦርቶዶክሳውያን ቀሳውስት በዚያ ጨለማ ዘመን የነበሩ ጠላቶች የሚነጋገሯቸውን ሐሳቦች እየተረዱ ህዝባቸውን ያነቁባቸውን ፈሊጦች ልንማራቸው የሚገባን መሆኑን ያሳየናል። በጨለማው ዘመን የነበሩት አባቶቻችን ከላይ ከተገለጹት እሴቶች በቀር ስንልክ እንኳ አልነበራቸውምና።

የነበረን ማህበራዊ ግንኙነት አቅም ከራሳችን ተሻግሮ በሩቅ ለነበረው ሁሉ ምሳሌ እንደነበረ "The trail leads us high up to where we get a breathless view of the astounding Ethiopian religion, which gives us the answer to many strange and incomrehensible traits in the Ethiopian to day"(page 4) በማለት ገልጸውታል፡፡ "which gives us the answer to many strange and incomrehensible traits" ብለው በተናገሩት ሐረግ ሊገልጹት የሞከሩት አሁን ሶሻል ሚድያ ለበጎ ተብሎ ከቀረበልን ፈሊጥ ይልቅ ቤተ ክርስቲያናችን የተጠቀሙችባቸው የድሮ ዘዴወች ሰፊና ምጡቅ እንደሆነ ለመግለጽ ያደረጉት ሙከራ ነው፡፡

Haggai Erlich የተባሉ እኛን ያጠኑ ጸሐፊም (the cross and the river page 68) በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፋቸው "In time this modern wing of the Coptic community would develop its own Ethiopian ideas, quite ddifferent from those of the patriarchet, the Holy Synod, and the Coptic Church establishment" ብለው መስክረዋል።

ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያናችን በሲኖዶስ ከመመራቷ በፊት በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ሊቃውንቷ በምትመራበት ጊዜ፣ በህዝቡ ላይ ያንዣበበውን መከራና ሞት ከህዝቡ በፊት በመሞት ያከናወኑባቸው እሴቶች በሲኖሶዶስ እየተመሩ በቅኝ ገዥወች ይቀጠቀጡ የነበሩት አኀት አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ይመኙት እንደነበረ የሚመሰክር ነው፡፡

በ North America እና በቀሩት አፍሪካ አገራት ይካሄዱ የነበሩትን ወረራወች እየተቃወሙ ስለነጻነት ይታገሉ የነበሩት ጥቂት ምእራባውያን ክርስቲአኖች "Liberation theology calls the affluent of the world not only to stand in solidarity with the poor and the oppressed , but ultimately to become like Christ the Lord, who for our sake he became poor, so that by his poverty we mught become rich (2 Corintians 8; 9) (Liberation Thelogy page 16) በሚለው ቅዱስ ጳውሎስ በገለጸው ሐዋርያዊ ትውፊት ላይ መንፈሳዊ ተጋድሏቸውን መሥርተው ያደረጉት እንቅስቃሴ የእኛን አባቶች ምሳሌ አድርገው እንደነበር በሰፊው ተነግሯል፡፡

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ኢትዮጵያውያን እስከ ሰማእቱ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያን ከወራሪወች እየተከላከሉ ለማቆየት የተጠቀሙባቸው እሴቶች (ሚድያወች) ከላይ የተገለጹት በዓለም የተደነቁ አደረጃጀቶች ነበሩ፡፡ ከዮቶር አመራሩን ተቀብሎ ሙሴ ህዝቡን ያደራጀበትን የቀደሙ አባቶቻችን እንደ ምሳሌ የተጠቀሟቸው ድርጅቶች (እሴቶች)፦ ማለትም በሰንበቴ በጽዋ ማሕበራትና በመቃብያን ስልቶች ምትክ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰጠው ትውፊት በ1964 ዓ/ም ሰማእቱ ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ ሰብስበውና አጠቃለው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናቸውን ባዲስ አወቃቀር በበሰበካ ጉባዔ ካደራጁት በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው "መልካሙን ገድል ተጋድለው ሩጫቸውን ጨርሰው ሃይማኖታቸው የተሰጣቸውን አደራ ጠብቀው የተዘጋጅላቸውን የጽድቅ አክሊል በሰማእትነት ተቀብለው አልፈዋል፡፡(2 ጢሞ 4፡7_8)

ፓትርያርክ ቴወፍሎስ ሰበካ ጉባዔውን የመሠረቱበት ምክንያትና ዓላማ ከዚህ በታች የተጠቀሰው ነው፡፡

በ1953 ዓ/ም በነ ጀነራል መንግሥቱ ንዋይ ተወጥኖ የነበረው መንግሥታዊ ለውጥ ከከሸፈ ወዲህ ኢትዮጵያን ያስጠበቁባቸው አገር በቀል ትምህርት ውስጥ የነበሩት እሴቶች እየደበዘዙ ወጣቱ በአስኳላው ትምህርት በአገር በቀሉ ትምህርት እየተተካ መምጣቱን ሰማእቱ ፓትርያርክ ቴወፍሎስ ተመለከቱ፡፡

ኢትዮጵያን የሚገልጿት የድሮወች ሊቃውንት በሞትና በእርግና እየተመናመኑ በአስካላው ተማሪ ብዛትም እየተዋጡ መምጣታቸውን አዩ፡፡ ያስኳላ ተማሪወች የውጭ መምህሮቻቸው የሚግቷቸውን እንዳለ በመቀበል ቤተ ክርስቲያናችን ወራሪወችን የተከላከለችባቸውን እሴቶች ሁሉ ሳይለዩ መታረም ከሚገባው ንጉሣዊ ስሕተት ጋራ በመፈረጅ ደርበው እንደሚመቷቸው አወቁ፡፡

አንዣቦ የመጣውን የጥፋት ማእበል አስቀድመው የተረዱት ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ፡ ኢትዮጵያን በፋኖነት በጎበዝ አልቃነትና በአርበኝነት ሲያስጠብቁ የነበሩት የጽዋ ማህበራትና ሰንበቴወች ወደ አንድ ተሰባስበው ተደራርበ በመምጣት ላይ ያለውን መከራ መመከት እንዲችሉ ዘመኑ በሚጠይቀው አወቃቀር ቤተ ክርስቲያንን በሰበካ ጉባዔ አደራጀት፡

ሙሴ በዮቶር አመራር ሕዝቡን በ12 ቁጥር አደራጅቶ የመራበትን ዮቶራዊ ምሳሌ የድሮ አባቶቻችን በመጠቀም በዘመናቸው የገጠሟቸውን ትግዳሮቶች የተቋቋሙባቸውን የሰንበቴ የጽዋ ማሕበራት እንደነበሩ አይተናል። ሰማእቱ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ በዘመናቸው እየተምዘገዘገ ሲመጣ በሩቁ ያዩትን የመከራ ማእበል ቤተ ክርስቲያናቸው መቋቋም እንድትችል፡ የነበሩትን ዮቶራውያን ድርጅቶች በቅዱስ ጳውሎስ ሐዋሪያዊ ትውፊት ባዲስ አደረጃጀት ከዚህ በታች በምጠቅሰው ሐዋርያዊ ትውፊት ቤተ ክርስቲያናቸውን አዋቀሯት።

*"ሰልፋችሁ ከሰማይ በታች ካሉት ከክፉወች አጋንንትና ከጨለማ አበጋዞች ጋራ ነውና በሁሉ የተዘጋጃችሁ ሁኑ ። ክፉወች አጋንንትና የጨለማ አበጋዞችን መቃወምና ድል መንሳት እንድትነሱ የእግዚአብሄር ጋሻ ያዙ። ወገባችሁን በጽድቅ ታጥቃችሁ ቁሙ። የጽድቅንም ጥሩር ልበሱ። የጋለውን የሰይጣንን ፍላጻ ሁሉ ማጥፋት ትችሉ ዘንድ የሃይማኖይ የጦር መሳሪያ ያዙ። የመንፈስ ሰይፍ በጃችሁ ያዙ። በራሳችሁም የሚያድነውን የራስ ቁር ድፉ" (ኤፌ 6፡12 17)።*

በቅዱስ ጳውሎስ የተገለጸውን ሐዋርያው ትውፊት፡- ፓትርያርኩ በአካላዊ ቁመናቸው የተሸከሟቸው የመዋጊያ የጦር ዕቃነታቸውን ከዚህ በታች በዝርዝር እገልጻለሁ።

"የጋለውን የሰይጣንን ፍላጻ ሁሉ ማጥፋት ትችሉ ዘንድ የሃይማኖት የጦር መሳሪያ ያዙ" እንዳለው ከራሳቸው እስከ ጥፍራቸው የተቀዳጇቸው በሕዝበ ክርስቲያን ላይ የሚነደውን እሳት ሁሉ ለማጥፋት ይችሉ ዘንድ ፓትርያርኩ የታጠቋቸው በሃይማኖት በሞራል በጥበብና በእውቀት ላይ የተመሠረቱ መንፈሳውያን መከላከያና መዋጋያ የጦር ዕቃወችን የሚያንጸባርቁ አመልካቾች (እማሬወች) ናቸው ።



በምስሉ እንደሚታየው ፓትርያርኩ በራሳቸው የደፉት፡- ቅዱስ ጳውሎስ "የሚያድነውን የራስ ቁር በራሳችሁም ድፉ" ያለውን መመሪያ በማድረግ ሕዝበ ክርስቲያኑን ከተሰነዘረበት ጥፋት ለማዳን የዲያብሎስን አበጋዞች በግዚአብሔር ኃይል መቃወምና ድል መንሳት እችላለሁ ብለው በመማል ነበር። በቀኝ እጃቸው የጨበጡት መስቀልም የሚያሳየው ቅዱስ ጳውሎስ "ክፉወች አጋንንትና የጨለማ አበጋዞችን መቃወምና ድል መንሳት እንድትነሱ የእግዚአብሄር ጋሻ ያዙ" ብሎ ያዘዘውን የሚገልጽና የሚያስገነዝብ የሃይማኖትና የሞርል ጋሻ ነበር።

"የመንፈስ ሰይፍ በጃችሁ ያዙ" እንዳለው ባህረ ኤርትራን በብትሩ ከፍሎ እስራኤላውያንን እንዳሻገራቸው እንደ ሙሴ ፓትርያርኩ በመከራ ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን የገባበትን መከራ በሞት ሽረት ታግለው ያሻግሩት ዘንድ በግራ እጃቸው የጨበጡት በትረ ክህነት ነበር። "ወገባችሁን በጽድቅ ታጥቃችሁ ቁሙ" እንዳለውም፡- የዘር ማጥፋት ግፍ የተፈጸመበት ህዝበ ክርስቲያን ተገቢውን ፍርድ ያገኝ ዘንድ ፓትርያርኩ ከአድላዊነት ራሳቸውን አግልለው በህዝቤ ላይ የዘር ማጥፋት ጥቃት ተፈጸመበት ብለው ለሚመለከተው ሁሉ እንዲያቀርቡ ነበር።

በዘመናችን ያሉት ፓትርያርክ በተሸከሟቸው ይልቁንም አቡነ ጳውሎስ ከሳቸው በፊት ያልነበሩትን መጠሪያወች ደራረበው ራስ (ጭንቅላት) ሆነው የተሰለፉባቸውን መላ አካላት ከዚህ በታች ለመግለጽ እሞክራለሁ።

<u>ሀ፡-በመቃጠል ላይ ያሉት ገዳማት ፓትርያርኩ ራስ ናቸው፡</u>

ለ፡-ከ 60 ሚልዮን በላይ ለሆነው ሕዝበ ክርስቲያን ፓትርያርኩ ራስ ናቸው።

ሐ፡-ለ80 ብጹአን ጳጳሳት (ሲኖዶስ) ራስ ናቸው።

መ፡-የደብረ ሊባኖስ እጨጌ (ራስ )ናቸው።

ሠ፡-የአኩስም ሊቀ ጳጳስ (ራስ) ናቸው።

ረ፡-በአዲስ አበባ ከተማ ላሉት ሁሉ አድባራት አልቆች ራስ ናቸው ።

ሰ፡-የቤተ ክህነቱ የመምሪያወች የበላይ ሐላፊ ራስ ናቸው።

ሸ፡-በየደብሩ በየገዳማቱና በየሀገረ ስብከቱ የደረሰውን ጉዳት የተፈጸመውን ልማት በመቃኘት ወሳኝ የሆነ ድምጽ ለሚሰማበት በመንበረ ፓትርያርኩ ለሚደረገው የአመታዊው ጠቅላላ ጉባኤ መሪ ራስ ናቸው።

በ፡-የሃይማኖቶች ተቋም የበላይ ጠባቂ ራስ ናቸው።

በቤተ ክርስቲያንችን መኅበራዊ ሚድያን በማሳደግ እንዴት ለበጎ ነገር "ዕቃ ጦር" ማድረግ የተዘጋጀውን ስልት ስመለከተው፡ ከላይ በፓትርያርኩ ስምና አካላዊ ቁመና የተገለጹት ለማሕበራዊ ሚድያነት መዋቀራቸውን ባለማስተዋል መሰለኝ።

የጥንት አባቶቻችን በዮቶር አመራር በስንበቴ በጽዋ ማህበራትና በመቃብያን ምሳሌ ኢትዮጵያ ውያንን አዋቅረው አጥርና ጋሻ ሆነው ኢትዮጵያን ከወራሪወች ያተርፉባቸውን እሴቶችንና በመቀጠልም ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ሁሉንም አጠቃለው ያዋቀሩበትን የሰበካ ጉባዔ ዓላማ የተገነዘቡ አልመሰሉኝም።

ቢረዷቸውማ ኑሮ፡- ቀደም ብለው በዮቶር ምክር ሙሴ ያደራጃቸው ምሳሌወች የሰንበቴ የጽዋ ማህበራትና ሰበካ ጉባዔኤ እንደ ጠፍ ጨረቃ ዳብዛቸው ከመታየት በቀር ከፓትርያርኩ ጀምሮ የቤተ ክህነቱን መዋቅር በተቆጣጠሩት በጳጳሳት በደብር አለቆችና በቀሳውስቱ መሰበራቸውን ይገነዝቡ ነበር።

በመንበረ ፓትርያርክ ፡ በመንበረ ጵጵስና ፡በደብር ልቅና በወርቅ ግምጃ ተዘናነተው የተቀመጡትን፡ የተቀመጣችሁበት መንበር ለህዝበ ክርስቲያኑ ሚድያ እንድትሆኑ እንጅ ለናንተ ሊቅነት ማእርግ መግለጫ አይደለም እያሉ በመንገር፡ ከፓትርያርኩ ጀምሮ እስከ ደብር አለቆች የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ከህዝቡ መካከል ወምበሩን እያነሱ ከደርቅ መሬት ላይ ቁመው የህዝቡን ብሶት በተባበረ ድምጽ ማስተጋባት ግዴታቸው እንደሆነ ይናገሩ ነበር፡

ሶሻል ሚድያ ከፍተው ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚናገሩ ሰወችም ከፓትርያርኩ ጀምሮ የቤተ ክህነቱን መዋቅር የተቆጣጠሩትን ጳጳሳት የደብር አለቆችንና ቀሳውስቱን "በመካከላችሁ የዋሆች ሆነን እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችን እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ"(1 ተሰ 2፡8) የሚለውን ሐዋርያዊ ትውፊት በተግባር መፈጸም እንዲገባቸው መናገር ነበረባቸው።

ከፓትያርኩ ጀምሮ እስከ ደብር አለቆች ለግል ጥቅማቸውና ለሚደግፏቸው የፖለቲካ ቡድኖች ቅድሚያ በመስጠት በየክልሉ የሚፈጸመውን የህዝበ ክርስቲያኑን እልቂት ባፈኑበት ወቅት፡ በየግላቸው ዩቱብ ከፍተው ስለ ቤተ ክርስቲያን መቃጠል ህዝበ ክርስቲያን መገደል መናገራቸው ቢያስመሰግናቸውም፡- አንዳንድ ዩቱበሮች የቤተ ክርስቲያናችንን ቀኖና በመረዳትም ይሁን ባለማዋቅ ወይም ጳጳሳቱ በሚዘርፉት ገንዘብ ከሚጠቀሙት ከጳጳሳቱ የሥጋ ዘመዶቻቸው ጋራ በመተባበር የሚያሰሙት ድምጽ ችግሩን በተገቢውና በሚመጥን መንገድ ባለማቅረባቸው የህዝበ ክርስቲያኑ የዋይታ ድምጽ እንዳይሰማ በማፈን የመከራውን ዘመን እያራዘሙት ነው።

በወርቅ ግምጃ በተሞካሸ ወንበር በሚንደላቀቁት በፓትርያርኩ በየክልሉ ጳጳሳትና በየደብሩ አለቆች ላይ፡ ሕዝቡ ተቆጥቶ እስካሁን ያስገደላችሁን በቃችሁ ብሎ እንዲነሳ ከማድረግ ይልቅ፡ በዘርና በቋንቋ ሴራ የሰከሩ ዩቱበሮች ከቀኖናችንና ከነገረ መለኮት ጋራ በሚጋጭ ቋንቋ የህዝበ ክርስቲያኑን ዋይታ እየሸፈኑበት ነው።

የፓትርያርኩን በደል ለመሸፈን የሚጥሩ  በዘረኝነት ስሜት የተጠቁ አንዳንድ ዩቱበሮች “በእጀ መስቀል ብቻ ነው ያለኝ እያሉ ቅዱሱ ፓትርያርካችን አለቀሱልን” በማለት ፓትርያርኩን ከፓትርያርክነት ወደ አንዲት ተስፋ ቆርጣ ቁጭ ብላ ወደ ምታለቅስ እመበልትነት በማውረድ ከላይ ከገለጽነው  ተልእኳቸው ጋራ ፓትርያርኩን እያጋጯቸው ነው፡፡

በየክልሉ ያሉትን ጳጳሳት የሚደግፉት ዩቱበሮችም፡ ጳጳሳቱ “በመካከላችሁ የዋሆች ሆነን  እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችን እናካፍላችሁ ዘንድ  በጎ ፈቃዳችን ነበረ”(1 ተሰ 2፡8) የሚለውን የሐዋርያዊ  ተልእኮ ግዴታቸውን ከመፈጸም ይልቅ፡ በሕዝበ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን መታረድ መቃጠልና መሰደድ የሩቅ ተመልካቾችና መርዶ ሰሚወች ሆነው በቅንጦት መንበራቸው ቁጭ ብለው ህዝቡን ለማታለል ስለራሳቸው ልብ መሰበር የሚያወሩትን ለሕዝበ ክርስቲያን በመቆርቆር ያዘኑ ለማስመስል “ጳጳሱ ዝምታቸውን ሰበሩ” እያሉ ስለተሰበረው ልባቸው “ሰበር ዜና” እያሉ መግለጫ  ለህዝብ ያሰማሉ፡፡

በህሰተኞች ዩቱበሮች የደነዘዘው ሕዝብም በፊቱ ስለወደቀው ወገኑና ስለራሱ መሞት ማልቀሱን አቁሞ፡ በብልጽግናው መንግሥት መሪ በጠቅላይ ምንስቴር ዓቢይ እንደበግ እየተነዱ የገቡት እነአቡነ ሳዊሮስ የሚያታልሉበትን ያዞ እንባ ለህዝበ ክርስቲያን አዝነው ከአንጀታቸው ፈንቅሎ ይወጣ እንባ አስመስለው እያቀረቡት ነው፡፡ የዋሑ ሕዝበ ክርስቲያኑም ለሱ ያለቀሱለት እየመሰለው  “ውይ! ውይ! የኛ ብጹዕ አባታችን ስለኛ መጎዳት ብጹዕ ልብቸው ተሰበረ፡፡ ከብጹአን ዓይኖቻቸው ብጹዐን እንባወች ፈሰሱ !” እያለ ስለ ልበ ሰባራወች ጳጳስት እንዲያለቅስ  እያደረጉት ነው፡፡  ከላይ የተገለጸውን የፐትርክናውን ሐላፊነትና ግዴታ ሳይረዱ  በወያኔወች ተነድተው ገቡተው ቁጭ ብለው ስለሚያለቅሱት ፓትርያርኩም  “ውይ! ውይ! ስለኛ  ቁጭ ብለው የሚያለቅሱት ደጉ ! ቅዱሱ! ፓትርያርካችን ከቅዱሳን ዐይኖቻቸው ቅዱሳን እንባወቻቸው  ፈሰሱብን! የኛ ዓይኖች ይፍሰሱለዎ !” እያሰኙት ናቸው፡፡

ያለአቅምና ያለችሎታ በኮታ እየተነዳ ወደ ቤተ ክህነት የገባው ስብስብ፡ ሲኖዶስ አለ እንዲባል ብቻ በተሰበሰበ ቁጠር ከቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ኩነት ውጭ ከመንግሥት በተሰጠው መነጋገሪ ተሰብስቦ በሚያሰማው ጫጫታ በመሞት ላይ ሆኖ የሚጮኸውን የህዝቡን ጩኸት እያፈነው ነው፡፡  በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሴራ ፖለቲካ አራጋቢ ዩቱበሮች ሲኖዶስ ተሰባሰበ በተባለው ጊዜ ሁሉ ይህንኑ አፋኝ ጫጫታ “ቅዱስ ሲኖዶሱ መንግሥትን  ግድያውን እንዲያቆም የሚያባብል ቅዱስ መግለጫ ሰጥቷልና እልልበሉ” እያሉ ሌት ተቀን በሚያሰራጩት አደንቋሪና አደናባሪ ስርጭታቸው ህዝቡ በራሱ ላይ የሚደርስበትን መጨፍጨፍ ረስቶ  “የኛ ቅዱስ ሲኖዶስ ቅዱስ ውሳኔ ወሰነልን”  እያሉ በማዘናጋት በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ የተደራረበ ደባ እየፈጸሙ ናቸው፡፡

<u>ካጠመቀቻችው ሕዝበ ክርስቲያን አልፋ ተርፋ ለጠቅላላው ኢትዮጵያዊ ዜጋዋ አንደበት (ሶሻል ሚድያ) ሆና ስትታገል የኖረች ቤተ ክርስቲያናችን ረሷን በራሷ አፍና ከገጸ ምድር እንድትጠፍ በተደረገችበት በዚህ ዘመን “በኦርቶዶክሳውያን ካህናትና መምህራን መካከል የማሕበራዊ ሚድያ  እውቀትን፤ መግባባትን፤ አንድነትን፤  ሕሊናነትንና ሞራላዊነትን በማሳደግ  መኅበራዊ  ሚድያ ለበጎ ነገር እንዴት “ዕቃ ጦር”) ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል ለማሳየት ይጥራል”</u> የሚል መመሪያ ለካህናቱ ያቀረበው አካል ተቀሰቀሱብኝ ብየ ከላይ ላቀርብኳት ጥያቄየ ምን ይመልስልኝ ይሆን?

ዩቱበሮች ሆይ! የእግዚአብሄር ቁጣ በህዝብ ላይ የሚነደው ቅዱስ ጳውሎስ “ማንም በንቱ ንግግር አያታላችሁ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ በእንደዚህ አይነት ነገር ነው”(ኤፌ 5፡6) እንዳለው ከቀኖናውና ከነገረ መለኮቱ ርቃችሁ ተራ የካድሬ ንግግራችሁ ህዝቡን ማወዛገባችሁን እባካችሁ አቁሙ!

ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ሆይ! “በማእበል ወደ ፈተና እየተነዳን ብልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ በሰወችም ረቅቅ ተንኮልና ማታለል ወዲያን ወዲህ እየተንሳፈፍንና እተገዋለልን ሕጻናት አንሁን”(ኤፌሶ 4፡14) ብሎ በተናገረው በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምክር እማጸናችኋለሁ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ማእበል ያለው በአየር ቀውስ የሚነፍሰውን ነፋስ አይደለም፡፡ እኛ አሁን የገባንበትን ከመንግሥትና ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያናችን አንደበቶች    የሚጎርፈውን አወዛጋቢ የሴራ ወሬ ነው፡፡ ስለዚህ በልዩ ልዩ የካድሬ ወሬወች ማእበል እየተገፋን የምናደርገውን ጫጫታ እናቁምና “ሶሻል ሚድያ ለበጎ” ብለው የተሰለፉትን ወገኖቻችን  የተሰበረው ሚድያችን ወደነበረበት ወደ ጥንቱ እንዲመለስ  ጠንክረው ትግላቸውን ከቀጠሉ የምንደግፋቸው መሆናችንን እንገልጽላቸው፡፡

ይቀጥላል